**ለመራጩ መመሪያ፡** ለአንድ ሰው ድምጽ ለመስጠት ከስሙ በስተግራ ያለውን **ክብ ያጥቁሩ**። በድምጽ መስጫ ጥያቄ ላይ ድምጽ ለመስጠት ከ"አዎ" ወይም "አይ" ቀጥሎ ያለውን **ክብ ያጥቁሩ።** እርሳስ ወይም ብዕር ብቻ ይጠቀሙ። ስህተት ከሰሩ፣ የምርጫ ካርዱን መልሰው ይስጡ እና አዲስ ይቀበሉ። በእያንዳንዱ ውድድር ከተፈቀደው በላይ ድምጽ አይስጡ።

**ለፕሬዚዳንት መራጮች**

**አንድ ፓርቲ** መምረጥ ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።

---**ሃሪስ እና ዋልዝ መራጮች**
ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
**ሜሪ ሱዛን ላርሰን**
**ዶን ላርሰን**
**ላሪ አልሰን**

---**ኦሊቨር እና ቴር ማአት መራጮች**
ሊቤርቴርያን (የነጻነት ፓርቲ)
**ራንዲ "ኡሪያ" ሉዋሊን**
**ግሪጎሪ ባልድዊን**
**ብራያን ዴዮንግ**

---**ትራምፕ እና ቫንስ መራጮች**
ሪፓብሊካን ፓርቲ
**ማርቲ ጃክሊይ**
**ክሪስቲ ኖም**
**ላሪ ሮደን**

---**ኬኔዲ፣ ጁኒየር እና ሻናሃን መራጮች**
ኢንዲፔንደንት (ገለልተኛ) ፓርቲ
**ጆርዳን ቶማስ**
**ጃሬድ ደግራፍ**
**ኤድዋርድ ዳይክስታራ**

**ለዩናይትድ ስቴትስ ተወካይ**

**አንድ** ብቻ መምረጥ ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።

---**ሼረል ጆንሰን**
ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
---**ደስቲ ጆንሰን**
ሪፐብሊካን ፓርቲ

**ለየሕዝብ አግልግሎት ኮሚሽነር**

**አንድ** ብቻ መምረጥ ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።

---ፎረስት ዊልሰን
ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ
---ኤ. ጊዲየን አክስ
ሊቤርቴርያን (የነጻነት) ፓርቲ
---ክርስቲን ፊገን
ሪፐብሊካን ፓርቲ

ሀ ይህ የናሙና ድምጽ መስጫ ነው።





**ለስቴት ሴናተር**
**ዲስትሪክት 15**
**አንድ** መምረጥ ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።
--- **ጄሚ ስሚዝ**
ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
---**ብሬንዳ ላውረንስ**
ሪፐብሊካን ፓርቲ

**ለስቴት ተወካይ**
**ዲስትሪክት 15**
**አንድ** መምረጥ ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።

--- **ኤሪክ ማኪ**
ዴሞክራቲክ ፓርቲ
**ኬደን ዊትማን**
ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
**ጆኒ ቼተር**
ሪፐብሊካን ፓርቲ
**ብራድ ሊንድወርም**
ሪፐብሊካን ፓርቲ

**ለአጠቃልይ ካውንቲ (አውራጃ) ኮሚሽነር**

እስከ **ሁለት** ድምጽ መስጠት ወይም ባዶ መተው ይችላሉ።

--- **ዲን ኢ ካርስኪ**
ሪፐብሊካን ፓርቲ
--- **ኮል ሃይሴ**
ሪፐብሊካን ፓርቲ
--- **አኒ ሊበንጉድ**
ገለልተኛ

**ፖለቲካዊ ያልሆነ ድምጽ መስጫ**

**የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛውን ማቆየት**

በእያንዳንዱ ዳኛ ላይ ድምጽ ይስጡ። ጃንዋሪ 1, 2025 ጊዜው የሚያበቃው በዚህ የምርጫ ካርድ ላይ የተጠቀሰው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በስልጣን ይቆይ ወይ?

ዳኛ ስኮት ፒ. ሚረን፣ የአምስተኛውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዲስትሪክት ወኪል

--- አዎ

---አይ

ለ ከዋናው የድምጽ መስጫው ካርድ ሊለይ ይችላል።





**ፕሪሲኒክት (አካባቢ) - 0518**

**የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ኢ**

<u>**ርዕስ**</u>፡ የሳውዝ ዳኮታ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ለተወሰኑ ባለሥልጣኖች እና ግለሰቦች ስሞች ጋር የሚያያዙ የሥርዓተ-ፆታ ማጣቀሻዎችን በማዘመን ላይ።

<u>**የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-**</u>

የደቡብ ዳኮታ ሕገ መንግሥት በ1889 ስቴቱ ዩናይትድ ስቴትስን በተቀላቀለበት ጊዜ ተግባራዊ ሆነ። እሱ፣ የእሱ እና እሱ የተለመደው የወንድ ተውላጠ ስሞች በግዛቱ ሕገ መንግሥት ጽሑፍ ውስጥ የተወሰኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ወይም ግለሰቦችን የማጣቀስ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ይህ ማሻሻያ የተወሰኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ወይም ግለሰቦችን በሚመለከት የተለመዱ የወንዶች ተውላጠ ስሞችን በማስወገድ የክልሉን ሕገ መንግሥት ጽሑፎችን ይለውጣል። ለምሳሌ የስቴቱ ገዥ ውይም ጋቨርነሩን ሲጠቀስ “እሱ የክልሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይሆናል” ከማለት ይልቅ ጽሑፉ ተቀይሮ “ገዢው/ዋ ወይም ጋቨርነሩ/ሯ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይሆናል/ትሆናለች” ተብሎ ይነበባል [የአማርኛው የሥርዓተ-ፆታ ማጣቀሻዎች አተረጓጎም ተካቶበታል]። ማሻሻያው በገዥው ወይም ጋቨርነሩ ላይ ሌሎች ማጣቀሻዎችም ሆነ ወይም ሌሎች የቢሮ ሃላፊዎችን የስም ማጣቀሻ፤ ማለትም እንደ ሌተናንት ገዥ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞችን ጨምሮ ሌሎች ባለስልጣኖች ላይ ተመሳሳይ ለውጦች አድርጓል። ማሻሻያው በህገ መንግስቱ ውስጥ በተጠቀሱት እንደ ሰዎች፣ መራጮች፣ እና መኮንኖች ያሉ ማጣቀሻዎች ላይም ተመሳሳይ ለውጦች አድርጓል።

---አዎ ማሻሻያውን ለማፅደቅድ "አዎ" የሚለውን ድምጽ ይስጡ።

---አይ "አይ" ድምጽ የስቴቱን ህግ እንዳለ ለመተው



SAMPLE

## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ኤፍ

<u>ርዕስ</u>፡ ይህ የሳውዝ ዳኮታ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ የሜዲኬይድ መስፍፋትን ተከትሎ ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙ ግለሰቦች ስራ መስራት የማስገደድ መብት ለስቴቱ ይሰጣል።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-</u>**

የሜዲኬድ ፕሮግራም በስቴት እና በፌደራል መንግስት የሚደገፍ፣ ለተወሰኑ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ለፕሮግራሙ ብቁ ለሚሆኑ ሰዎች የህክምና ሽፋን የሚሰጥ ነው። እ.ኤ.አ. በ2022፣ መራጮች የሜዲኬይድ ብቁነት ለማንኛውም በእድሜ ከ18 በላይ እና ከ65 በታች እንዲሁም ገቢያቸው ከፌዴራል ድህነት ደረጃ ከ133 በመቶ በታች ለሆነ ማንኛውም ግለሰብ፣ በተጨማሪ የፌዴራል ድህነት ደረጃ 5 በመቶ ለሆነ ቤተሰብ ተደራሽ የሚያደርጉ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን አፅድቀዋል።

ይህ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኞች ከሆነ ግለሰብ በስተቀር በተስፋፋው የሜዲኬይድ ፕሮግራም መሠረት ጥቅማጥቅሞችን ለመቀበል ብቁ በሆነ ሰው ላይ የሥራ መስፈርቶችን እንዲያስገድድ ስቴቱን ያስችለዋል። ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያው በሚዲኬይድ መስፋፋት ምክንያት ብቻ ተጠቃሚ በሚሆኑ ግለሰቦች ላይ ሊያስገድድ የሚችለው የተወሰኑ የስራ መስፈርቶች የሉም ። በስቴቱ የሚቀርበው ማንኛውም የሥራ መስፈርት ከመተግበሩ በፊት በፌዴራል መንግሥት መጽደቅ አለበት።.

---አዎ "አዎ" ድማፅ ማሻሻያውን ለመቀበል።

---አይ "አይ" ድምጽ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌውን እንዳለ ለመተው



## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ጂ

<u>ርዕስ</u>፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት ውስጥ ፅንስ የማቋረጥ መብትን ለመደንገግ የተጀመረ ማሻሻያ።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-</u>**

ይህ የተጀመረው ማሻሻያ ፅንስ የማስወረድ ሕገ መንግሥታዊ መብትን እና የፅንስ ማቋረጥን መብት የመቆጣጠር የህግ ማዕቀፍ ይዘረጋል። ይህ ማዕቀፍ ፅንስ ማቋረጥን የሚመለከቱ ነባር ሕጎችን እና ደንቦችን ይሽራል።

ማሻሻያው በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ የአንዲት ነፍሰ ጡር ሴት የፅንስ ማቋረጥን ውሳኔ, እና የፅንስ ማቋረጥን በማካሄድ ላይ ባለው ሂደት የህግ ክትትልም ሆነ ማንኛወ የህግ ድንገጋን ይከለክላል።

ከሶስት እስከ ስድስት ወር ባለው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ ማሻሻያው የአንዲትን ሴትን የፅንስ ማቋረጥ ውሳኔ እና የፅንስ ማቋረጥ የማከናወን ጉዳይ በህጉ ደንብ እንዲወሰን ይፈቅዳል። በነዚህ ወራቶች ውስጥ ማንኛውም የአንዲት እርጉዝ ሴት የፅንስ ማቋረጥ ውሳኔ ወይም የፅንስ መቋረጥ አመክንዮ ከአካላዊ ጤናዋ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት ።

ከስድስት እስከ ዘጥኝ ወር ባለው ጊዜ የአንዲት ሴትን ነፍስ ለማዳን ወይም ጤናዋን ለመጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ማሻሻያው የህጉ ደንብ እንዲከበር ወይም የፅንስ ማቋረጥ ክልከላ እንዲያደርግ ይፈቅዳል። በነዚህ የመጨረሻ የርግዝና ወራት የፅንስ ማስወረድ አስፈላጊ መሆን አለመሆን በእርጉዟ ሴት ሐኪም እና ሙያዊ ፍርድ መወሰን አለበት.

የፍርድ ቤት ማብራሪያ በማሻሻያው ላይ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የሕግ አውጭው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ድንጋጌዎችን መለወጥ አይችልም

---አዎ ማሻሻያውን ለመቀበል "አዎ" የሚለውን ድምጽ ይስጡ።

---አይ ሕገ መንግሥቱን እንደአለ ለመተው "አይ" ድምጽ ይስጡ።





## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ኤች

<u>ርዕስ</u>፡ በደቡብ ዳኮታ ህገ-መንግስት የዋናው የስቴቱ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያገኙትን ሁለት የየትኛውም ፓርቲ ተወወካይ እጩዎች ወደ ሀገራዊ ምርጫ እንዲያልፉ ለማድረግ የሚያስችል ማሻሻያ።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-</u>**

በአሁኑ ጊዜ በአገራዊ ምርጫ ላይ ለመቅረብ የስቴቱ ታላቅ ፓርቲ እጩዎች እና የፓርቲው አባል መራጮች ብቻ በሚሳተፉበት ምርጫ ላይ የሚከተሉትን መሥሪያ ቤቶች ለመምራት መወዳደር አለባቸው፤ ገዥ ወይም ገቨርነር፣ ሕግ አውጪ፣ የዩኤስ ሴኔት እና የተወካዮች ምክር ቤት፣ እና የካውንቲ ቢሮዎች። ፓርቲው ምርጫውን ለሁሉም ፓርቲ አባላት ክፍት ካላደረገ በስተቀር፣ ተመራጮቹን መምረጥ የሚችሉት የተመራጮቹ የፓርቲ አባል የሆኑ መራጮች ብቻ ናችው። አነስተኛ ፓርቲ እጩዎች በራሳቸው ዋና ምርጫ ወይም በፓርቲ ጉባኤ ሊመረጡ ይችላሉ።

ከዋና ፓርቲዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው እጩዎች (ገለልተኛዎች) በአጠቃላይ የምርጫ መስጫ ወረቀት ላይ ለመቅረብ የእጩ ማመልከቻዎችን ብቻ ማቅረብ አለባቸው.

ከላይ ለተዘረዘሩት መሥሪያ ቤቶች፣ ይህ ማሻሻያ ለታጩበት መስሪያቤት እርስ በእርስ የሚወዳደሩበት፣ ሁሉንም እጩዎች የሚያካትት አንድ ዋና ምርጫ እንዲካሄድ የሚያደርግ ሲሆን፣ ተመራጮቹ የትልቁ፣ የትንሹ፣ ወይም የገለልተኛው ፓርቲ አባል መሆን ይችላሉ። እጩዎች የማንኛውንም የፓርቲ ደጋፊነትንም ሆነ አባልነት ከስማቸው ቀጥሎ በመጥቀስ በድምጽ መስጫው ላይ መዘርዘር ይችላሉ። ሁሉም መራጮች ለማንኛውም እጩ ድምጽ መስጠት ይችላሉ። ብዙ ድምጽ ያገኙ የመጀመሪያ ሁለቱ እጩዎች ለጠቅላላ ምርጫ ያልፋሉ። ለአንድ ቢሮ የሚመረጡት ከአንድ በላይ እጩዎች ካሉ፣ ወደ አጠቃላይ ምርጫ የሚሄዱት እጩዎች ቁጥር ከሚመረጠው ቁጥር በእጥፍ ይበልጣል።

ዋና ምርጫዎች ለሌሎች ቢሮዎች ሊደረጉ ይችላሉ።

ማሻሻያው ሕገ መንግሥታዊ በሆኑ መስፈርቶች ሊገመገም ይችላል።

**<u>የፊስካል ማስታወሻ፡-</u>**
ክፍት የሆኑ ዋና ምርጫዎች ለአንድ ድምጽ መስጫ በ0.47 ዶላር ተጨማሪ የድምፅ መስጫ ካርዶችን ማሳተም አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም የስቴት አውራጃዎች የዚህ አይነት የምርጫ አጠቃላይ ወጪ $23,667 ይሆናል። የእያንዳንዱ አውራጃ የጠቅላላ ወጪ ድርሻ ይለያያል። ከስቴቱ መንግስት የሚጠበቅ ወጪ የለም።

---አዎ ማሻሻያውን ለመቀበል "አዎ" የሚለውን ድምጽ ይስጡ።

---አይ ሕገ መንግሥቱን እንደአለ ለመተው "አይ" ድምጽ ይስጡ።



SAMPLE

## ጅማሪ እርምጃ 28

**<u>ርዕስ</u>፡** ለሰው ልጅ ፍጆታ በሚሸጥ ማንኛውም ነገር ላይ ታክስን የማስቆም እርምጃ።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡</u>**
በአሁኑ ጊዜ ስቴቱ ምግብ እና መጠጦችን ጨምሮ በተወሰኑ ምርቶች ሽያጭ ወይም አጠቃቀም ላይ ግብር ይሰበስባል። ብዙ የከተማ አስተዳደሮችም ይህንን ግብር ይሰበስባሉ።

ይህ እርምጃ ስቴቱ በሽያጭ ወይም ለሰው ፍጆታ በሚውል ማንኛውም ክፍያ ላይ ታክስ እንዳይሰበስብ ይከለክላል። እርምጃው እነዚህን የስቴቱ የገቢ ምንጮች ያስቀራል።

የሰው ልጅ ፍጆታ በስቴቱ ህግ ትርጉም የተሰጠው ነገር አይደለም። ሆኖም፣ የተለመደው ፍቺው ከምግብ እና ከመጠጥ ውጭ ሌሎች ነገሮችንም ያካትታል።

እርምጃው ከአልኮል መጠጥ ሽያጭ ጋር የተያያዘ ታክስ ወይም በተዘጋጁ ምግቦች ላይ ግብር ማስከፈልን አይከለክልም። የተዘጋጀ ምግብ ህጋዊ ትርጉም ተሙቆ ወይም በመቢያ ዕቃዎች የሚሸጥ ምግብን ያካትታል።

እርምጃው የስቴቱን ከትምባሆ ጋር የተያይዙ ማስተር ስምምነቶችን እና አብሮ በተሳለጠው የሽያጭ ታክስ ስምምነት ስር ያሉትን የመንግስት ግዴታዎች ሊያዛባ ይችላል። ይህ ማስተር ስምምነት ሲጋራ ማጨስ በሕዝብ ጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳትን አስመልክቶ ብዙ-ስቴቶችን ያካተተ በሲጋራ አምራቾች ላይ የተፈፀመ ክስ ውጤት ነው። የሳውዝ ዳኮታ የዚህ ማስተር ስምምነት አመታዊ ድርሻ ወደ 20 ሚሊዮን ዶላር ይደርሳል። ይህ ስምምነት ብዙ ስቴቶችን ያካተተ፤ በብዙ ስቴቶች አስተዳደር ስር ትንባሆ ለሚሸጡ ኩባንያዎች የሽያጭ አሰባሰብ እና የአጠቃቀም ታክስን ለማቃለል የተነደፈ ፕሮግራም ነው።

የፍርድ ቤት ወይም የህግ አውጭ ማብራሪያ በእርምጃው ላይ አስፈላጊ ይሆናል.

የፊስካል ማስታወሻ፡-

ከጁላይ 1፣ 2025 ጀምሮ፣ ስቴቱ ከአልኮል መጠጦች እና ከተዘጋጁ ምግቦች በስተቀር ለሰው ልጅ ፍጆታ ከሚሸጥ ማንኛውንም ሽያጭ በዓመት 123.9 ሚሊዮን ዶላር የቀረጥ ገቢ ቅናሽ ሊደርስበት ይችላል። የከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ግን ለሰው ፍጆታ የሚሸጥ ማንኛውንም ነገር መቅረጥ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

---አዎ "አዎ" ድማፅ እርምጃውን ለመቀበል።

---አይ "አይ" ድምጽ የስቴቱን ህግ እንዳለ ለመተው

*ሀ ይህ የናሙና ድምጽ መስጫ ነው።*

## ጅማሪ እርምጃ 29

**<u>ርዕስ</u>፡** የማሪዋና እንደመዝናኛ አጠቃቀምን፣ ይዞታን እና ስርጭትን ህጋዊ የሚያደርግ ጅማሪ እርምጃ።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-</u>**
ይህ የተጀመረው እርምጃ ዕድሜያቸው 21 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች ማሪዋና የማሳደግ፣ የመጠቀም፣ የማከፋፈል እና ማሪዋና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶችን እንዲይዙ ያስችላቸዋል። ግለሰቦች ከማሪዋና ንጥረነገሮች ከሚገኙም ሆነ ሌላ የማሪዋና ምርቶች በስተቀር እስከ ሁለት አውንስ ማሪዋና ሊይዙ ይችላሉ። ግለሰቦች እስከ ስድስት የሚደርሱ የማሪዋና እፅዋት ወይም በአንድ ቤተሰብ ከአስራ ሁለት የማይበልጡ እፅዋት ሊኖራቸው ይችላል። እርምጃው በሌሎች የማሪዋና እና የማሪዋና ምርቶች ይዞታ ላይ ገደቦችን ያስቀምጣል።
በእርምጃው መሰረት፣ ማሪዋና የማሳደግ፣ የመጠቀም፣ የማከፋፈል እና የማሪዋና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ይዞ መገኘት ከ21 አመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ህገወጥ ሆኖ ይቆያል። በማሪዋና ተጽእኖ ስር ማሽከርከር ህገወጥ ነው። እንደ ትምህርት ቤቶች ትንባሆ የተከለከለባቸው ቦታዎች ላይ የግለሰቦችን ማሪዋና ይዞ መገኘትንም ሆነ መጠቀምን እርምጃው በጥብቅ ይገድባል። እርምጃው አሰሪዎች የሰራተኛውን ማሪዋና አጠቃቀም እንዲገድቡ ያስችላቸዋል። የህንፃ ባለቤቶች በንብረታቸው ላይ የማሪዋና አጠቃቀምን መቆጣጠር ይችላሉ።
እርምጃው ከሄምፕ (ማሪዋና) ጋር በተያያዙ የስቴት ህጎች ላይ ተጽእኖ አያመጣም። እንዲሁም የስቴቱን ማሪዋናን ለህክምና የማዋልፕሮግራምን ህጎችን አይቀይርም።
እርምጃው በስቴቱ ህግ መሰረት በወንጀል ቁጥጥር ስር ያሉ ከማሪዋና የተገኙ ንጥረ ነገሮችን ህጋዊ ያደርጋል። በፌዴራል ሕግ ማሪዋና ሕገ-ወጥ እንደሆነ ይቆያል።
የዚህ እርምጃ የዳኝነት ወይም የህግ አውጭ ማብራሪያ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል.

የፊስካል ማስታወሻ፡-
እርምጃው የካናቢስ ሽያጭን ከህገወጥነት ባያስቀርም ነገር ግን የካናቢስ መጠቀሚያ ቁሳቁሶች ሽያጭን ህጋዊ ስለሚያደርግ ስቴቱ እና የከተማ አስተዳደሮች አነስተኛ ተጨማሪ የሽያጭ ታክስ ገቢ ይሰበስባሉ። በመሆኑም የስቴቱ አውራጃዎች የእስር ቤት ወጪዎቻቸው በየአመቱ በ$581,556 ሊቀንስ ይችላል።

---አዎ እርምጃውን ለማፅደቅድ "አዎ" የሚለውን ድምጽ ይስጡ።

---አይ "አይ" ድምጽ የስቴቱን ህግ እንዳለ ለመተው

*ለ ከዋናው የድምጽ መስጫው ካርድ ሊለይ ይችላል።*

**ፐሪሲኒክት (አካባቢ) - 0518**

## የተመላከተ ህግ 21

**<u>ርዕስ</u>፡** የቀጥታ (የቧንቧ) ስርጭት መስመር ተቋማትን ለመቆጣጠር፣ የአውራጃ አስተዳደሮች በተወሰኑ የቧንቧ መስመር ኩባንያዎች ላይ ተጨማሪ ክፍያ እንዲያስከፍሉ ለመፍቀድ እና ለመሬቱ ባለቤቶች መብት የህግ ደንብ ለማስቀመጥ የሚያስችል አዲስ የህግ ድንጋጌ መስፈርቶችን ለማቅረብ የተመላከተ ህግ።

**<u>የጠቅላይ አቃቤ ህግ ማብራሪያ፡-</u>**
ካውንቲዎች (አውራጃዎች) የቧንቧ መስመር ኦፕሬተሩ የታክስ ክሬዲት (ስጦታ) በሚቀበልበት ማንኛውም የግብር አመት፣ በካርቦን ዳይኦክሳይድ ቧንቧዎች ላይ ለአንድ ጫማ (30 ሴንቲ ሚትር) የቧንቧ ርዝመት 1.00 ዶላር እንዲከፍሉ ይህ የተመላከተው ህግ ይፈቅዳል።
የቧንቧ መስመር የተዘረጋበት እያንዳንዱ የመሬት ንብረት ባለቤት እንደ ታክስ ማካካሻ ሆኖ ከዚህ ተጨማሪው ክፍያ የሚገኘውን ገቢ መከፋፈል አለበት። ማንኛውም ቀሪ ገቢ እንደ እያንዳንዱ ካውንቲ ምርጫ ሊከፋፈል ይችላል። ከንብረት ታክስ፣ ወይም ከመንገድ ስምምነቶች ጋር የተያያዙ ክፍያዎች በስተቀር ሌላ ምንም አይነት ክፍያ በባለ ንብረቱ ላይ ሊደረግ አይችልም።

በተጨማሪም ሕጉ በካርቦን ዳይኦክሳይድ ቧንቧዎች ላይ የተወሰኑ አስገዳጅ መስፈርቶችን ያስቀምጣል፡- የቧንቧ መስመሮች በአነስተኛ ጥልቀት መቀበር አለባቸው፤ እያንዳንዱ የቧንቧ መስመር ኦፐሬተር በቧንቧው ምክንያት ለሚደርሰው የቧንቧ ንጣፍ እና የመሬት ንብረት ላይ አደጋ ተጠያቂ ነው፤ እያንዳንዱ ኦፐሬተር ለቧንቧው ፍሳሽ ማንጠባጠብ ወይም ብልሽት ተጠያቂ ነው፤ እንዲሁም ማንኛውም የኦፐሬተሩ የመሬት ንብረት ተወካይ የቧንቧ መስመር ኦፐሬተር ተቀጣሪ መሆንን ጨምሮ የስቴቱ ነዋሪ፣ ወይም የስቴቱ ፈቃድ ያለው የሪል እስቴት ወኪል መሆን አለበት። ህጉ በተጨማሪም የካርቦን ቧንቧ መስመሮች ስምምነት በጽሁፍ እንዲሆኑ እና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚተገበሩ መስፈርቶችን ያካትታል። የቧንቧ መስመር ኦፐሬተሮች ስምምነት በተደረገ በአምስት ዓመታት ውስጥ የንግድ ሥራ መጀመር አለባቸው፤ አልያም ስምምነቱ ያለ ምንም ስራ አምስት አመት ከሞላው ውድቅ ይሆናል።.

---አዎ የህግ አውጭው ህግ ህግ እንዲሆን ለመፍቀድ "አዎ" የሚለውን ድምጽ ይስጡ።

---አይ የህግ አውጭውን ህግ ውድቅ ለማድረግ "አይ" የሚል ድምጽ ይስጡ።



SAMPLE